# ዝክረ ሰማዕታት

(በኢሕአፓነት መስዋእትነት ለከፈሉ)

ቃል ኪዳናችሁ መስዋዕትነት ሆኖ ቃላችሁን ስታከብሩ
መሃላችሁን በደማችሁ በነፍሳችሁ ስታጠነክሩ
ተጋድሏችሁ ባይወራም ባይነገር
እኔን እንደቋሚ የሚበላኝን ልናገር።
የእንባ ዘለላዎች ባይኖቼ አዝዬ
እምነቴን ከነፍሴ ጥጋት አንጠልጥዬ
ቁስል ውጬ ቁስል ከአንጀቴ ጨምሬ
ረስቸ፣ ዘንግቸ፣ ችላ ብየ እየመሰለኝ
እሪታችሁ እየቆጠቆጠኝ
ቀን በሰረቀ ቁጥር ከእንቅልፌ እባንናለሁ
በቁሜ እባትታለሁ።

በአጥንታችሁ ላይ ተራምጄ በወደቃችሁበት አፈር ቁሜ
ትዝታዬ መስዋዕትነታችሁ ሆኖ አንጀቴን እያላመጠው
የቃላችሁ ገደል ማሚቶ ጆሮየን እያስደነገጠው
ዳግም ትንሳኤ ከፊት ከፊቴ ሲናፍቀኝ
ከባቢየን ቃኝቼ የሰው ጥማት ልቤን ሲፍቀኝ
ከብርሃን ጉዞ ወደ ብርሃን ጠልማችሁ
ሳስብ ሳንሰላስላችሁ
ከእናንተ ጋር የጀምርኩት የብርሃን መንገድ
ከብርሃን ላይ ጥሎኝ ስንገዳገድ
ምናል እላለሁ ምን አል እንዴው
ሰውነቴም ዛሬም እኮ አወ ዛሬም
ተክዶብኝ ከምታመም
እኔም በብርሃን መንገድ እንደተጓዝኩ
ብርሃን ፈነጥቄ እንደናንተው ብጠልም።
አዲስ በአል በአሮጌ መንገታገት ታግቶ
በሚንፈራፈር በሚንደባለል ድርግም ታብቶ
እያየሁኝ ከምኖር
ምናል እኔም በአምፃ ተቀብሬ በነበር።

ባገኘሁ በተረፈኝ ቁጥር ደስ ባለኝ
በናንተ ደም ያላገጥሁ ያሾፍኩ እየመሰለኝ
መሃላችን እየከበደኝ
ቅር እያለ ሆድ ይብሰኛል
ድንጋጤ ያመኛል።

ተኝቼ አንቀላፍቼ
እረፍት አብዝቼ
ዘና ሲል ሰውነቴ
ይመጣና የፍርሃት ድብርቴ
ከአፋችን የወጣው መሃላ ከእስር ጉሮኖው ያዜምነው
በአረህ በጥሻው
ምነው አንተ ሰው አደራ አለብህ
ይለኛል
ለምን ችላ ትላለህ ትረሳለህ?
ስፀዳዳ ሲያምርብኝ ስሽልል፣ ስዘንጥና ስጎርስ
ይጠራኛል
የተካበው የአፅም ካብ የተንጣለለው የደም ደለል
ታቀብ አስብ እንጂ ይለኛል።
የሄዳችሁበት የመጨረሻ እስትንፋስ
በለስታና በዝግታ በህሊና ላይ ሲመላለስ
ዛሬም ማዕረጌን ሳይነፍገኝ
ጓድ ስማ ጓድ ብሎ ይጠራኛል።
የተንጣለለው የፋኖነት መርህ ጠንክሮ
የታጋይነት ብሥራት ውሎ አድሮ
የተቀባበልናት እውነት
ምንም ብታንስ የደም አዝርዕት እኮ ናት
ቃል ኪዳን የተግባባንበት።

አይኔን ገልጨ ሳስባችሁ
ብርሃኑን እያስተዋልሁ
በመኖሬ እቃጠላለሁ
ባለመሰዋቴ እበሽቃለሁ
አራለሁ እተክናለሁ።
የማገላበጠው ወረቀትና የምስማው ሳይጥመኝ
ወኔ ሲይዘኝ ሲዘልብኝ
የማማክረው ሲያንስብኝ
ተራ በተራ እያሰብኳችሁ
ከራሴ ጋር እኳረፋለሁ
ከኔው ጋራ እጣላለሁ
ከኔው ሙግት እገጥማለሁ
እኔኑ ራሴን እቀጣለሁ።

ነፃነት የሚል ቃል በተነገረ በተነበበ ቁጥር
እያተከነኝ የሚች መኖር
የህያዋን መቀብር
የቆራጦች ነፍስ መታጎል የጎበዛዝን ቅስም መስበር

የቁርጥ ቀን ጠንካሮች እያየሁ ታሪካችሁ ሲዳፈን
እንዴት ታዲያ እፎይ ልበል፣ እንዴት ልርሳ ተጋድሎችሁን።
ባደፈ አንሶላ ተጠቅልሎ
በትግል መሞት ተዘምሮ
እንዴት ልርሳ ተጋድሎችሁን
በጠባቦች የድንቁርና ተግባር
ተነድፎ የሚንገታገተውን።

ደቂቃ አልፎ ደቂቃ ሲተካ ህሊናየ እየሸፈተ
ከውስጤ አልፎ እኔኑ እየጠየቀ
ከኔው ጋር እየተዳረቀ
እኔኑ እያበሸቀ
ምን እያረግህ ነው እያለኝ
በአፅንዖት ሲጠይቀኝ
ምንነቴ ከናንተ ጋር ስላልወደቀ
በቆራጥነት ስላላቀ
መልስ አጥቼ እባንናለሁ
አንዳንድ ጊዜ ራሴን እጠለዋለሁ
ረሴን እንቀዋለሁ
በራሴ ራሴ እነዳለሁ።

በዚህ የኑሮ ሽርሽር
በዝቶ የውሸት ትርምስና ግርግር
ቀያችሁ በተነሳ ቁጥር
የወደቃችሁለት አገር
አልነጋ ላላ ውድቀት ላጠለመው ኢትዮጵያዊነት መንደር
ፍቅር እንዳይሞት ስትጥሩ
ሙትቻ ጋር በነፍስ ትንንቅ ስትዳጭሩ
ህዝብ እንዳይናቅ
ኢትዮጵያዊነት እንዳይወድቅ።

ጣት በጆሮየ ላይ ሲያንቃጭል
መሥርዕ ከፊቴ እየመጣ
ሳላውቀው ምልክት እሰራለሁ
በአደባባይ ላይ እንደዋልሁ
የእንባ ምንጭ አነባለሁ
እየተደበቀሁ አለቅሳለሁ።

ስራመድና ስቀመጥ አካሌ መሬት ሲነካ
ይናገረኛል አፈሩ
ምነው? ይለኛል ምድሩ

ምነው? ይለኛል በትዝብት
ምንድን ነህ? አንተ በእውነት
ይጠይቀኛል ነፋስ አየሩ
ሕዋ ጠፈሩ።

ምለሃል እኮ ይለኛል
ደማቸውን ኮትኩተህ ፅጌረዳዋን ልትንከባከብ
የደሃን እንባ ልትጠርግ ነፃነትም እንዲያብብ
ምልሃል እኮ ይለኛል
በመርህ በመተክልህ ፍዳን ልትቆጥር
አበሳን ልትጋፈጥ ግንባርህን ሳታጥፍ ልትኖር።
ፀሐይቱን ስመለከታት
ጨረቃ ፊቴን ስትነካው
ዝናብ በላዩ ሲያካፋ
ነፋስ ገላየን ሲዳስሰው
ትዝታ ይወቃኛል።
ነፍሴና ስጋየም እስ በሳቸው ሲነካኩና ሲጣሉ
ጉልበቴ ሲያንስ ሲደክም
ቃላችሁን ይዤ ሳልቆም
ልወድቅ መስሎኝ እፈራለሁ
ቃል ኪዳኔን አስበዋለሁ።

ይህንን ሁሉ በውስጤ እያላመጥሁ
መስዋእትነታችሁን እየኖርሁ
እናንት በስርቀት ተነስታችሁ
ለመሃላችሁ ለኖራችሁ
ለቃላችሁ ለተሰዋችሁ
ነፍሴ ዝክረ ሰማዕታት ሆናለች
ሰላምታ
ሰማዕታት።
(እምነት እስተዳር)